# የቤተሰብ አባላት መልካም የእርስ በእርስ ግንኙነት ለመልካም የህፃናት አስተዳደግ

## ማውጫ

አጠቃላይ መመሪያ....................................................................................2

የስልጠናው አላማ....................................................................................5

ክፍል አንድ፡- መልካም የቤተሰብ ግንኙነት ለህፃናት አስተዳደግ ያለው ጠቀሜታ..............................5

ቁልፍ መልእክቶች....................................................................................15

ክፍል ሁለት፡- ወላጆች እንዴት መልካም የቤተሰብ ግንኙነትን ማበልጸግ ይችላሉ?..........................16

ቁልፍ መልእክቶች....................................................................................25

## የስልጠናው አጠቃላይ መመሪያ

የስልጠናው ዋና አላማ ፡ በስልጠናው መጨረሻ ወላጆች/አሳዳጊዎች የቤተሰቡን አባላት የእርስ በእርስ ግንኙነቶች ለመልካም የህፃናት አስተዳደግ እንዲረዱ ምን ማድረግ እንደሚገባ ይገነዘባሉ።

የስልጠናው ተሳታፊዎች

የስልጠናው ተሳታፊዎች እንዲሆኑ የሚጠበቁት መምህራን፣ ህፃናትን በሚንከባከቡ ድርጅቶች የሚሰሩ ሰራተኞች፤ እንዲሁም ወላጆች እና አሳዳጊዎች ናቸው።

ያለፈውን ቀን ውይይት መከለስ

በየስልጠናው መጀመሪያ ላይ ሁለት ተሳታፊዎች እየተመረጡ ባለፈው ስልጠና የተማሩትን ፍሬ ሀሳቦችን እንዲናገሩ በአወያዮች/በአስልጣኞች ይጠየቃሉ። ለምሳሌ

ባለፈው የተወያየንባቸው ነገሮች ምን ምን ነበሩ?

ባለፈው ከተወያየንበት ርእሰ ጉዳይ አንፃር በቤታችሁ ከልጆቻችሁ ጋር ምን አደረጋችሁ? ያጋጠማችሁ ችግር ነበር ወይ?

ያለፈውን ትምህርት ለጎረቤቶቻችሁ አካፈላችሁ?

ቅድመ እና ድህረ ስልጠና ምዘና

ያለፈውን ስልጠና ለማስታወስ ከሚደረገው ተግባር ቀጥሎ የእለቱ ስልጠና ከመጀመሩ በፊት ለተሳታፊዎች የቅድመ-ስልጠና ምዘና ይሰጣቸዋል ። በስልጠናው የቀሰሙትን እውቀት ለመገምገም ደግሞ የድህረ-ስልጠና ምዘና በያንዳንዱ ስልጠና መጨረሻ ላይ ይሰጣል።

አጠቃላይ የስልጠና ደንቦች፤

- አወያዮች በስልጠናው የመጀመሪያ ቀን የሚከተሉትን የስልጠና ደንቦች ለተሳታፊዎቹ ያሳውቋቸው፤
- የሰልጣኞች አቀማመጥ በግማሽ-ክብ ቢሆን እንደሚመረጥ ማሳወቅ
- የአወያይ እና የተሳታፊዎች ትውውቅ ማካሄድ
- በሰአት መገኘት

- በስልጠናው ወቅት ሞባይል ስልክ መዝጋት/ድምጽ አልባ ማድረግ
- በእያንዳንዱ የስልጠና ክፍለ-ጊዜ ጊዜ መገኘት፣
- ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፣
- የሌሎች ሰዎችን ሃሳብ ማክበር፣

- የአስታዋሽ ምርጫ፡ በየእያንዳንዱ ቀን መጀመሪያ ላይ ባለፈው ቀን የተማሩትን ትምህርት በተመለከተ ለተሳታፊዎች ለማስታወስ በአጭሩ ገለፃ የሚያደረጉ ሁለት ተሳታፊዎችን መሰየም፡ 5 ደቂቃ የማቅረቢያ ጊዜን መወሰን፣
- የስልጠና ቦታውን ማስተካከል - በየእያንዳንዱ ቀን መጀመሪያ ላይ ለአስር ደቂቃ ያህል የስልጠናው አስተባባሪዎች የስልጠናውን ቦታ ያመቻቻሉ፣
- ሰአት ተቆጣጣሪ መምረጥ፣

የሚያስፈልጉ ቁሶች

- በህፃናት እድሜ ደረጃ የተዘጋጁ የተረት ወይም የታሪክ መፅሃፍት እና ስእሎች
- ኤል ሲ ዲ ፕሮጀክተርና ኮምፒውተር (ከተቻለ)
- ንፁህ የመፃፊያ ሰሌዳ / ፍሊፕ ቻርት
- ማርከር
- ብዕር እና የማስታወሻ ደብተር
- በራሪ ፅሁፎች

በእየንዳንዱ ስልጠና መጨረሻ አወያዮች/አሰልጣኞች ማስታወሻ መያዝ አለባቸው

በያንዳንዱ ስልጠና መጨረሻ ላይ አወያይ ስለ ውይይቱ ሂደት ማስታወሻ እንዲይዙ ይጠበቃል። ለውይይቱ በሚያደርጉት ዝግጅት ወይንም በውይይት ሂደት ውስጥ ነጥረው የወጡና በዚህ ምእራፍ ውስጥ ሊካተቱ ወይም በድጋሚ ሊጤኑ የሚገቡ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ መያዝ ያስፈልጋል። እነዚህ ፍሬ ሀሳቦች ይህንን ሰነድ ወደፊት የበለጠ ለማሻሻልና ለማዳበር ይረዳሉ።

## የቤተሰብ አባላት መልካም የእርስ በእርስ ግንኙነት ለመልካም የህፃናት አስተዳደግ

ይህ ስልጠና የቤተሰብ አባላት የእርስ በእርስ ግንኙነትን መልካም ማድረግ ለመልካም የህፃናት አስተዳደግ እንዴት እንደሚረዳ መሠረታዊና ዝርዝር የሆኑ መረጃዎችን ያስጨብጣል።

<u>መርሃ-ግብር</u>

| ይዘት | የማስተማሪያ ዘዴ | ሰዓት |
|---|---|---|

| | | |
|---|---|---|
| የቅድመ-ስልጠና ምዘና | የጥያቄ ወረቀቶቹን መበተን | 15 ደቂቃ |
| የስልጠናው አላማ | ማንበብና መወያየት | 4 ደቂቃ |
| ጤናማ የቤተሰብ ግንኙነትና ለህፃናት አስተዳደግ ያለው ጠቀሜታ | ጥያቄና ፣መልስእና ገለፃ | 50 ደቂቃ |
| ቤተሰቦች እንዴት መልካም የቤተሰብ ግንኙነትን ማሳደግ ይችላሉ? | ጥያቄና ፣መልስ እና ገለፃ | 50 ደቂቃ |
| ቁልፍ መልዕክቶች | ማንበብ እና መወያየት | 20 ደቂቃ |
| የድህረ-ስልጠና ምዘና | የጥያቄ ወረቀቶቹን መበተን | 15 ደቂቃ |

## ክፍል አንድ፡ መልካም የቤተሰብ ግንኙነት መኖር ለህፃናት አስተዳደግ

## ያለው ጠቀሜታ

ለውይይቱ የተመደበው ጊዜ ፡ ስድሳ ደቂቃ

### የውይይቱ አላማ

- በውይይቱ መጨረሻ ተሳታፊዎች ጤናማ የቤተሰብ ግንኙነት ለህፃናት አስተዳደግ ያለውን ጠቀሜታ ይረዳሉ

ቤተሰብ ምንድነው**?**

ቤተሰብ በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ስብስብ ነው። ህፃናት ደህንነት ተሰምቷቸው፣ ከፍርሀት ነፃ ሆነውና የማወቅ ጉጉታቸውን በብቃት ተጠቅመው የአእምሮ ብስለታቸውንና ማህበራዊ ክህሎታቸውን የሚያዳብሩበት የመጀመሪያ ትምህርት ቤት ቤተሰብ ነው።

አወያይ ቤተሰብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያብራሩላቸው

## ቤተሰብ በእነማን ይመሰረታል?

- አንድ ቤተሰብ በአብዛኛው በእናት በአባት እና በልጆች ይመሰረታል
- ከላይ ከተጠቀሱት ጋር ሌሎች የቅርብ ዘመዶችን በማካተት፤ ለምሳሌ አጎት ወይም አክስት፤ አያት ወይም ሌሎች ዘመዶች ሊያካትት ይችላል
- ወላጆች ተለያይተው ከሆነ ቤተሰቡ በአንድ ወላጅና በልጆች የተገነባ ይሆናል
- አልፎ አልፎ ሁለቱም ወላጆች ከሞቱ ወይም ከተሰደዱና ሌላ የቅርብ ዘመድ በማይኖርበት ወቅት ቤተሰቡ በልጆች ብቻ የተመሰረተ ይሆናል።
- በበጎ ፈቃደኛ አሳዳጊዎች ወይም በህፃናት ማሳደጊያ ድርጅቶች ውስጥ የሚመሰረት ቤተሰብም ይኖራል።

አወያይ

እንደሚታወቀው አብዛኛውን ጊዜ ቤተሰብ እናትና አባት እንዲሁም ልጆችን ያካትታል። በሀገራችንና በሌሎችም በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት እንደሚታየው በቤተሰብ ውስጥ አጎት ወይም አክስት፤ አያት ወይም ሌሎች የወላጅ የቅርብ ዘመዶችም አብረው እየኖሩ ቤተሰብ የሚመሰረትበት አጋጣሚ ብዙ ነው።ወላጅ በተለያየ ምክንያት በማይኖርበት ጊዜ ሌሎች ዘመዶች፣ አያቶች፣ አጎቶች፣ አክስቶች፣ እህቶች ወይንም ወንድሞች ልጆችን ያሳድጋሉ።

አልፎ አልፎ ከወላጆች ሁለቱም ከሞቱ ልጆች ብቻቸውን ይቀራሉ፤ ቤተሰቡም በልጆች ብቻ የተመሰረተ ይሆናል። በዚህ አይነት አጋጣሚ ታላላቅ ልጆች ታናናሽ ልጆችን ያሳድጋሉ።

የቅርብ ስጋ ዘመድ በማይኖርበት ጊዜ ህፃናት በበጎ ፈቃደኛ አሳዳጊዎች ወይም በህፃናት ማሳደጊያ ድርጅቶች ውስጥ በሚመሰረት ቤተሰብ ውስጥ ሊያድጉ ይችላሉ።

ይህንን ለተሳታፊዎች ያስረዱ

መልካም የቤተሰብ አባላት የእርስበርስ ግንኙነት ምንድነው?

መልካም የቤተሰብ የእርስበርስ ግንኙነት አለ የሚባለው በቤተሰብ አባላት መካከል እርስ በእርስ ግልፅነት፣መተሳሰብ፣ መከባበርና መንከባከብ ሲኖር ነው። በመልካም የቤተሰብ የእርስ በእርስ ግንኙነት እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ደስተኛ ነው። በቤተሰቡ አባላት መካከል ልዩነቶች ወይም ቅሬታዎች ሲኖሩ በግልጽነት ያለ ጥላቻ ወይንም ሃይልን ሳይጠቀሙ በጓደኝነትና በገንቢ ስሜት ውይይት በማድረግ መፍትሄ ማበጀት የመልካም ግንኙነት መገለጫ ነው

አወያይ፡- እንዲህ በማለት ያስረዱ፡

በመልካም የእርስ በእርስ ግንኙነት ግልፅነት ወሳኝና አስፈላጊ ነው። በሰዎች መሃል ሁልጊዜም የፍላጎት ወይም የሀሳብ ልዩነቶች እንዲሁም ቅሬታዎች ይኖራሉ። ነገር ግን የፍላጎት ወይም የሀሳብ ልዩነቶች እንዲሁም ቅሬታዎችን በግልጽነት፣ ያለ ጥላቻ ወይንም ሃይልን ሳይጠቀሙ፣ በጓደኝነትና በገንቢ ስሜት ውይይት በማድረግ መፍትሄ መፈለግ የመልካም ግንኙነት መገለጫ ነው። መልካም ግንኙነት ባለበት ቤት ሰዎች ጊዜያቸውን በአንድነት ያሳልፋሉ።

በመልካም የቤተሰብ ግንኙነት ወላጆች፡-

- ለልጆቻቸው ፍቅርን በመለገስ በየእለቱ አቅሮ በማበረታታት እንዲሁም ንፅህናቸውን በመጠበቅ፣ በአግባቡ መመገባቸውን፣ ዘወትር ጤናማ መሆናቸውንና ሰላማዊ እንቅልፍ መተኛታቸውን ያረጋግጣሉ።
- ልጆቻቸውን ለማነጋገር፣ ለማድመጥና ታሪክ ለመንገር ጊዜ ይሰጣሉ። በመልካም ቤተሰብ ውስጥ ወላጆች ህፃናትን ለማረም አካላዊ ቅጣት አይጠቀሙም። በምትኩ ገና ከጠዋቱ ጀምረው እንደ አንድ ሆነው ልጆችን አቅጣጫ በማስያዝ በጠንካራ አመራር ክትትል በማድረግ ልጆች የሚፈለግን ጠባይ እንዲይዙ ይመራሉ፣ ይቆጣጠራሉ።
- ከልጆቻቸው ጋር ከቤት ውጪ እንቅስቃሴዎችን (ለምሳሌ የእግር ጉዞና ሽርሽር) አብረው ያደርጋሉ፣ ሬድዮ ያደምጣሉ እንዲሁም አብረው ይመገባሉ።
- በእራት ጊዜ ወላጆችና ልጆች በጠረጴዛ ዙሪያ እንዲወያዩና ግንኙነት እንዲኖራቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ።

መልካም የቤተሰብ ግንኙነት መኖር ለህፃናት ምን ይጠቅማል?

- ለህፃናት ማህበራዊ ህይወትን፣ ማህበራዊ ህግጋትንና ማህበራዊ ሀላፊነቶችን ለማስተማር
- ህፃናት ራሳቸውን በተለያየ የህይወት ክህሎት ለማበልፀግ
- ለአእምሮ ብስለት እና ማህበራዊ ክህሎት መዳበር
- ራሳቸውን ከተለያዩ አደጋዎችና ጥቃቶች ለመጠበቅና ለመከላከል፣
- ከቤተሰብ አባላት መልካል የእርስ በእርስ ግንኙነትን ለመማር
- ለመንፈስ ደህንነትና ለአእምሮ ጤናቸው መዳበር
- ህፃናት ሰላማዊ፣ በራሳቸው የሚተማመኑ፣ ጠንክረው ለመስራት አቅም ያላቸው፣ ችግርን የሚቋቋሙና የሚፈቱ ሆነው እንዲያድጉ።
- ህፃናት ራሳቸውን የተለያዩ የህይወት ጎዳናዎች ስኬታማ ለማድረግና የራሳቸውን ደህንነት ለመጠበቅ

አወያይ የመልካም የቤተሰብ ግንኙነት ለህፃናት መልካም እድገት የሚሰጣቸውን ጥቅሞች ለተሳታፊዎች ያብራሩላቸው።

የተሳታፊዎችን የልጅነት ጊዜን የሚያስታውሱ ጥያቄዎች

አወያይ
ይህ ተግባር በቤተሰብ አባላት ውስጥ ያለው የእርስ በእርስ ግንኙነት ለህፃናት አስተዳደግ ያለውን ጠቀሜታ በተመለከተ እንደሚሆን ለተሳታፊዎች ይግለፁ። በመቀጠልም ተሳታፊዎች ስለ ራሳቸው የልጅነት ወቅት እንዲያስቡና የሚከተለውን እንዲያስታውሱ ይንገሯቸው። በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ ለ 1 ደቂቃ ካሰቡ በኋላ 3 ተሳታፊዎች ብቻ ስለትውስታቸው መልስ እንዲሰጡ ይጋብዙ

ተሳታፊዎች ስለ ራሳቸው የልጅነት ጊዜ እንዲያስቡና እንደ ልጆች በቤተሰባቸው መካከል ስለ ነበረው ግንኙነት እንዲናገሩ ማድረግ። ስለልጅነታቸው ሲያስታውሱ፡-

ሀ. በቤተሰቡ ውስጥ በጣም አስደሳች የእርስ በርስ ግንኙነት የነበራቸውን ሁለት የቤተሰብ አባላት እንዲያስታውሱ ይጠይቋቸው።

ለ. በቤተሰባቸው ውስጥ በጣም የማያስደስት የእርስ በርስ ግንኙነት የነበራቸው ሁለት የቤተሰብ አባላት እንዲያስታውሱ ይጠይቋቸው።

ሐ. በልጅነታቸው ወቅት ከቤተሰባቸው ውስጥ ከሁሉም በበለጠ በጣም የሚያስደስት ግንኙነት የነበራቸው ከየትኛው የቤተሰብ አባል ጋር እንደነበር እንዲያስታውሱ ይጠይቋቸው።

መ. በልጅነታቸው ወቅት ከቤተሰባቸው ውስጥ ከሁሉ በበለጠ ሁኔታ የማያስደስት የእርስ በርስ ግንኙነት የነበራቸው ከየትኛው የቤተሰብ አባል ጋር እንደነበር እንዲያስታውሱ ይጠይቋቸው።

የተግባር ልምምድ፡ በቀረቡ ታሪኮች ላይ የሚደረግ የቡድን ውይይት

ለአወያይ

ተሳታፊዎች በአጫጭር ታሪኮች ላይ ተመርኩዘው ለሚቀርቡላቸው ጥቄዎች በጋራ ተወያይተው መልስ እንዲሰጡ ይጠበቃል።

- ተሳታፊዎች በሶስት ቡድን እንዲከፈሉ መንገር
- ለሶስቱም ቡድን ለእያንዳንዳቸው ታሪክ የተፃፈባቸው ሶስት ገፅ ወረቀቶች ይሰጣቸው።
- ለቡድኑ አባላት እያንዳንዱን ታሪክ በተመለከተ የቀረቡትን ሁለት ጥያቄዎች መመለስ እንዳለባቸውና ጥያቄውን ለመመለስም በገጠመኙ ላይ በቡድናቸው መወያየት እንዳለባቸው ይንገሩዋቸው።
- የእያንዳንዱን ቡድን ውይይት የሚመሩ ሰዎች ሊኖራቸው እንደሚገባ ይገለፅላቸው። ከተሳታፊዎች መካከል የውይይቱን ጭብጥ የሚፅፉና ለሁሉም ተሳታፊዎች የሚያቀርቡ ሰዎችን በማስመረጥ በተሳታፊዎች የሚሰጡ መልሶችን እንዲዘግቡ ያድርጉ።
- ተሳታፊዎች በቀረቡት ገጠመኞች ላይ በማተኮር በውይይቱ ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ እንዲያደርጉ እንዲሁም ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ይንገሯቸው።

ታሪክ አንድ- የስንቄ ቤተሰብ

ስንቄ የስድስት አመት ልጅ ስትሆን የአንደኛ ክፍል ተማሪ ናት። የስንቄ ወላጆች ሁልጊዜ ይጨቃጨቃሉ። በጭቅጭቃቸው ወቅትም እርስ በእርሳቸው የጥላቻ ቃላት ይለዋወጣሉ። የስንቄ አባት ባለቤታቸውን ሰነፍና የማትረባ በማለት ይሳደባሉ። የስንቄ እናትም ባለቤታቸውን ተመሳሳይ ስድብ ይሳደባሉ። አንዳንድ ጊዜም ጭቅጭቃቸው ወደ ድብድብ ያመራል። ባልና ሚስት ሲደባደቡ ዘወትር የስንቄ እናት ከስቃይ ብዛት ይጮሃሉ።

ስንቄ ከሁለት አመቷ ጀምሮ ይህንን ድርጊት ስትመለከት ነው ያደገችው። አንድ ቀን ስንቄ ከእናቷ ጋር ብቻቸውን ሲሆኑ እናትየው ለስንቄ አባቷ በጣም መጥፎና ክፉ ሰው እንደሆኑ ነገሯት። ቀጥለውም እርሷ ባትወለድ ኖሮ ይህ ሁሉ ስቃይ እንደማይደርስባቸውና እንዲህ እየተሰቃዩ ከአባቷ ጋር የሚኖሩት ለእርሷ ሲሉ እንደሆነ ነገሯት።

በሌላ ቀን ደግሞ ስንቄ ከአባቷ ጋር ብቻቸውን ሲሆኑ አባትየው ለስንቄ እናቷ ምን ያህል መጥፎና ሰነፍ ሴት እንደሆኑ ነገሯት። ስንቄንም እንደ እናቷ መጥፎ ሆና እንዳታድግ በማስጠንቀቅ ‹ይህ ሳይሆን ቀርቶ አንቺም እንደ እናትሽ ባለጌ ከሆንሽ እገርፍሻለሁ› አሏት።

ታሪክ ሁለት፡- የአበበ ቤተሰብ

አበበ የሚተዳደረው በአናጢነት ሙያ ነው። ባለቤቱ ጫልቱ ደግሞ የቤት እመቤት ናት። አበበና ጫልቱ ስድስት ልጆች አሏቸው። ትልቁ ልጃቸው አስር አመቱ ሲሆን የመጨረሻው ደግሞ ስድስት ወሩ ነው። አበበ ባተሌ በመሆኑ ዘወትር ጠዋት ልጆቹ ከእንቅልፋቸው ሳይነሱ ለስራ የወጣ ወደ ቤት የሚገባው ልጆች ከተኙ በኋላ ከምሽቱ ሶስት ሰአት በኋላ ነው። ጫልቱም ቀኑን ሙሉ በቤት ውስጥ ስራ ተጠምዳ ትውላለች። ለቤተሰብ ምግብ የምታዘጋጀው ብቻዋን ነው። በየእለቱ ውሃ መቅዳትና ለምግብ ማብሰያ እንጨት ማምጣት አለባት። የቤተሰቡ ልብስ ሲቆሽሽ ደግሞ በየእለቱ ልብስ ታጥባለች። ልጆቹ ብዙውን ጊዜ እርስ በእርሳቸው አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከጎረቤት ልጆች ጋር በመጫወት ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ። አበበ ከልጆቹ ጋር የሚገናኘው በበአላት ቀናት ብቻ ነው። ጫልቱ በቤት ውስጥ ስራ ስትሰራ ትንሹን ልጅ በጀርባዋ ታዝለዋለች። ስራ ሲበዛባት ደግሞ የዘጠኝና የስምንት አመት እድሜ ያላቸው እህቶቹ እንዲያዝሉት ታደርጋለች። አበበና ጫልቱ ሌላ ቦታ ሲሄዱ ልጆቹ የትና ከማን ጋር እንደሚውሉ አያውቁም።

ታሪክ ሶስት፡- የሸምሱ ቤተሰብ

ሸምሱ የስምንት አመት ልጅ ሲሆን ለወላጆቹም ብቸኛ ልጅ ነው። የሸምሱ ወላጆች ነጋዴዎች ናቸው። እናትና አባቱ የተለያዩ ሱቆች አላቸው። የሸምሱ ወላጆች በሱቆችና በቤት ውስጥ የሚሰሩ በርካታ ሰራተኞች አሏቸው። የሸምሱ ወላጆች በርካታ ዘመዶችና ጓደኞችም አሏቸው። የእነ ሸምሱ ቤት ዘወትር በእንግዶች እንደተሞላ ነው። ሁሉም ሰው ሸምሱን ይወደዋል። ሸምሱ ብዙ ጊዜ የሚተኛው ለአዳር ከሚመጡ እንግዶች ጋር ነው። የሸምሱ ዘመዶችና የቤተሰቡ ወዳጆች በየጊዜው ሸምሱን ወደ ተለያዩ ቦታዎች ይወስዱታል። ስለዚህም ሸምሱ ከእንግዶች ጋር ወጥቶ መዝናናት ያስደስተዋል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በዘመዶቹ ቤት ለቀናት ይቀመጣል።

አወያይ

የውይይቱ ተሳታፊዎች የቀረቡትን ሶስት ገጠመኞች ካነበቡ በኋላ እያንዳንዱ ቡድን የሚከተለውን ጥያቄ ስለእያንዳንዱ ታሪክ ይመልሱ ይመልሱ።

ለተሳታፊዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎች፤

1. በታሪኮቹ ውስጥ በቀረቡት የቤተሰብ አባላት መካከል ያለው ግንኙነት ለህፃናት እድገት መልካም ነው ወይንስ መልካም አይደለም? ለምን?

2. በታሪኮቹ ውስጥ በቀረቡት ወላጆችና ልጆች መካከል ያለው ግንኙነት ለህፃናት እድገት መልካም ነው ወይንስ መልካም አይደለም? ለምን?

አወያይ

የቡድን ውይይት ዘገባና ውይይት (ሃያ ደቂቃ)

ለእያንዳንዱ ቡድን ተወካይ ሶስት ደቂቃ ብቻ በመፍቀድ የቡድናቸውን መልስ እንዲያቀርቡ፤ እንዲሁም ሁለት ተጨማሪ ተሳታፊዎች አስተያየት እንዲሰጡ ወይንም ጥያቄ እንዲያቀርቡ ይፈቀዱላቸው።

አወያይ፡

በተሰጡ አስተያየቶች ላይ እርማት ወይም ማጠናከሪያ ይስጡ፤ ለዚህም እንዲረዳዎ ከዚህ በታች ያሉትን ማጠቃለያዎች ይጠቀሙ።

ስለ ስንቄ ቤተሰብ ታሪክ የተሰጠ ማጠቃለያ

የስንቄ ቤተሰቦች በመካከላቸው ጤናማ ግንኙነት የላቸውም። የስንቄ ቤተሰቦች ተደጋጋሚ ግጭትና ጥላቻ እያንዳንዳቸው ለዘመዴ መጥፎ ምሳሌ ሆነዋል። የስንቄ ቤተሰቦች ግጭት በዘመዴ ላይ ብዙ ፍርሃት ፈጥሮባታል። ስለዚህም ስንቄ ፈሪ ልጅ ሆና አድጋለች። ስንቄ ከወላጆቿ የተማረችው አለመግባባትን ለመፍታት ከሰላማዊ ውይይት ይልቅ ጡብኝነትን ነው። ወላጆቿ አንዳቸው ስለሌላቸው መጥፎነት እየነገሩ ያሳደጉበት ሁኔታ ለወላጆቿ አክብሮት ሳይሆን ጥላቻ እንዲኖራት፤ ከሌሎች ጋር ባላት ግንኙነትም ሁልጊዜ ሌሎችን መቅረብ የምትፈራና በሩቁ ብቻ ግንኙነት የምትፈጥር አድርጓታል።

ስለ አበበ ቤተሰብ ገጠመኝ የተሰጠ ማጠቃለያ

አበበ ለቤተሰቡ ገቢ ለማስገኘት ጥሩ ስራ በመስራት ላይ ይገኛል። ነገር ግን አበበ ከባለቤቱ ጫልቱ ጋር በመሆን ልጆቹን በአግባቡ ለመምራት የሚሆንምንም አይነት ጊዜ የለውም። ስለዚህም ልጆቹ በራሳቸው መንገድ እንዲሄዱ ትቷቸዋል። ልጆቹ ስለ ህይወት የነገራቸው፣ ምን ማድረግ እንዳለባቸው፣ ስለራሳቸው ምን ማወቅ እንዳለባቸው፣ ችግሮችን እንዴት መፍታት እንዳለባቸው፣ በተለያዩ ቦታዎች ሲገኙ ምን አይነት ጠባይ ማሳየት እንደሚገባቸው እንዲሁም ከተለያዩ ሰዎች ጋር እንዴት መቅረብ እንዳለባቸው ያስተማራቸው የለም። ህፃናቱ ለህይወታቸው እጅግ አስፈላጊ የሆነውን የወላጆቻቸውን  የቅርብ ክትትልና አመራር ማግኘት አልቻሉም።

አወያይ

ስለ ሽምሱ ቤተሰብ ታሪክ የተሰጠ ማጠቃለያ

የሽምሱ ቤተሰብ በየእለቱ ቡብዙ ሰዎች ይሞላል። ሽምሱ ብዙ ጊዜውን ከቤተሰቡ ጓደኞችና ከዘመዶቹ ጋር ያሳልፋል። እነዚህ ሰዎች ሽምሱን ከቤተሰቡ በበለጠ ተፅእኖ ሊያሳድሩበት ይችላሉ።  ሽምሱ ወደ መጥፎ ጠባይ ሊመሩት ከሚችሉ ሰዎች ጋር የመገናኘት እድሉ ሰፊ ነው።  ወደ ቤታቸው ከሚመጡት የተለያዩ ሰዎች ያየውንና የሰማው ነገር በአስተሳሰቡና በጠባዩ ላይ ተፅእኖ ይኖረዋል። በየጊዜው ከቤተሰቡ ጓደኞችና ዘመዶች ጋር ከቤቱ ወጥቶ ሲውልና ሲያድርም እንዲሁ ለብዙ ልማዶችና አመለካከቶች የተጋለጠ ነው። በዚህ አይነት አጋጣሚዎቹ የሽምሱ አስተዳደግ በመጥፎ ጎዳና እንዲሆን ሊያደርጉት ይችላሉ። ወላጆች ሽምሱ ከሌሎች እንግዶች ጋር የሚያሳልፈውን ጊዜ መገደብ ነበረባቸው። ወላጆቹ ሽምሱን በአግባቡ ለመምራት በቂ ጊዜ ስላልሰጡት ጥሩ ጠባይ ይዞ ማደግ እንዳይችል እንቅፋት ሊሆንበት ይችላል።

መልካም የሆነ የቤተሰብ ግንኙነት መለያዎች ምንድን ናቸው?

አወያይ

መልሱን ከመንገርዎ በፊት ተሳታፊዎች መልካም የሆነ ቤተሰብ ግንኙነት መለያዎቹ ምንድን ናቸው? በማለት ይቀው መልሳቸውን በሰሌዳ ያስፍሩ

መልካም የቤተሰብ ግንኙነት የተለያዩ መገለጫዎች

- ቤተሰቡ በመደበኛነት አብሮ የሚያሳልፋቸው ጊዜዎች አሉት።
- ወላጆች ያለማዳላት ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው እኩል ትኩረት ማግኘታቸውን ያረጋግጣሉ።
- ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች የህፃናትን እድገትና ጤና ለማነቃቃት ፍቅር ይሰጣሉ። በተጨማሪም አቅም በፈቀደ ሁሉ ተገቢ የእንክብካቤ እርምጃ ይወስዳሉ።
- የቤተሰብ አባላትና ልጆች በየጊዜው ይገናኛሉ። ለምሳሌ እርስ በእርስ በመተቃቀፍ በመካከላቸው ፍቅር እንዳለ ይሰማቸዋል።
- ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች ከህፃናት ጋር ሲሆኑ አይን ለአይን ግንኙነት፣ በመዳሰስና ምን ያህል እንደሚወዷቸው በመናገር ለህፃናት ፍቅርን ያሳያሉ።
- ቤተሰቡ ልጆች በተገኙበት ስለ ቤተሰብ፤ ስለ ማህበረሰብና ስለ ሀገር እንዲሁም ስለ አለም ገንቢ ውይይቶችን ያደርጋል፤ ሀሳብ ይለዋወጣል። ልጆች በአዋቂዎች መካከል ከሚደረገው ውይይት ብዙ ይማራሉ። በተቃራኒው በአዋቂዎች መካከል ያለው ግንኙነት ጤናማ ያልሆነና የማያስደስት ከሆነ ልጆች ፍርሀትንና ጥላቻን ይማራሉ።
- የቤተሰብ አባላት ለቤተሰቡ የበኩላቸውን አገልግሎት ይሰጣሉ። እድሜያቸው ከሶስት አመት በታች ከሆኑት ውጪ ሁሉም የቤተሰብ አባላት እንደየእድሜያቸውና እንደየአቅማቸው የሆነ

እገዛ ለቤተሰቡ ያደርጋሉ። ይህ በመሆኑም የቤተሰብ አባላት ተፈላጊነት ይሰማቸዋል፤ በዚህም ደስተኞች ይሆናሉ።

ልጆች በቤተሰብ ውስጥ የአባልነት ስሜት የሚሰማቸው፡-

- ራሳቸውን ነፃ ሆነው እንዲገልፁ ደህንነታቸውን በመጠበቅ ሲታገዙ፣ መሰረታዊ ፍላጎታቸው (ለምሳሌ አካላዊ፣ አእምሮአዊና ማህበራዊ) ሲሟላ እንዲሁም ፍቅር ሲሰጣቸውና የተለያዩ ጥቃቶች እንዳይደርሱባቸው ጥበቃ ሲደረግላቸው ነው።
- ልጆች ስለ ራሳቸው መልካም ስሜት እንዲሰማቸው ጥረት በሚያደርጉበት ወቅት ሲወደሱ ወይም ሲመሰገኑ ነው።
- ልጆች አንድን ነገር ማከናወን ሲያቅታቸው በስራቸው የራስ መተማመን ስሜት እንዲያዳብሩ ሲታገዙና ሲበረታቱ ነው።
- ልጆች ከቤተሰብ አባላትና ከቤተሰቡ ቅርበት ካላቸው ጋር እንዴት መግባባት እንዳለባቸው ሁኔታዎችን በማመቻቸት በሂደት ለማህበረሰቡና ብሎም ለአለም ፋይዳ ያላቸውን ነገሮችን እንዲያበረክቱ ሲታገዙ ነው።
- ልጆች ከሌሎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ትክክልና ስህተት፣ ተቀባይነት ያለውና የሌለው ተግባርን ልዩነት ማስተማር ተገቢ ነው። ይህም ልጆች ለጥቃት እንዳይጋለጡ እንዲጠነቀቁ ያበረታታቸዋል።
- አንድ የቤተሰብ አባል ለቤተሰቡ እርሱ የሚያደርገው ነገር ሲኖርና ያንን የሚጠበቅበትን ነገር አድርጎ ውጤታማ ሲሆን፤ሲመሰገን ትልቅ ደስታ ሰማዋል። በራስ የመተማመን ስሜቱም ይጎለብታል።

አወያይ

ሁለት ተሳታፊዎችን ይምረጡና በቤተሰብ አባላት መካከል ያለው ግንኙነት ለህፃናት ጤናማ እድገት የሚሰጠውን ሁለት ጥቅሞችን በአጭሩ እንዲያብራሩ ይጠይቋቸው።

**ቁልፍ መልእክቶች**

- ቤተሰብ የህፃናት ማህበራዊ አለም ወሳኝ ክፍል ነው።
- ቤተሰብ ህፃናት አለምን እንዲገነዘቡ የሚያስችላቸውን አካባቢና ተሞክሮ መፍጠር አለበት።
- ህፃናት ደስተኛ እንዲሆኑ በቤተሰብ አባላት መካከል ያለው ግንኙነት የመተሳሰብ፤ የግልፅነትና ችግሮችን/ቅሬታዎችን በሰላማዊ ውይይት የሚፈቱበት የሆነ መልካም ሁኔታ ያስፈልጋል።
- ህፃናት ለማደግ፣ ለመዳበርና ራሳቸውን በተለያዩ መንገዶች ለመጠበቅ ከተለያዩ ሰዎች ጋር መገናኘት ያስፈልጋቸዋል። ሆኖም ግን ከህፃናቱ ጋር የሚገናኙት ግለሰቦችን ባህርይና አመለካከት ወላጆች ሊያውቁት ይገባል።
- መልካም ግንኙነት ያለው ቤተሰብ ከልጆቹ ጋር የሚያሳልፈው ጊዜ በጠብ ሳይሆን በሰላማዊ ክርክር፣ በጨዋታና በውይይት ነው።
- ወላጆች ወይንም ሞግዚቶች ለልጆቻቸው እንክብካቤና ፍቅር መስጠት አለባቸው። የሚሰጧቸው ፍቅር ተመሳሳይነት ያለው እንጂ በየወቅቱ የሚለያይ መሆን የለበትም
- በመልካም የቤተሰብ ግንኙነት ውስጥ ወላጆች ወይንም ሞግዚቶች ከልጆች ጋር ሲያወሩ አይን ለአይን በማየት፣ በመዳበስና በመያዝ/በመሸከም ፍቅር ሊሰጧቸው ይገባል።
- አያቶች፣ ወንድምና እህቶች፣ ጎረቤቶችና የወላጆች ጓደኞች ህፃናት ለሚኖራቸው ፍቅር፣ ትስስርና የቤተሰብ አባልነት ስሜት አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። ይሁን እንጂ ልጆች ከዘመዶቻቸውና ከጓደኞቻቸው የሚያገኙትን መረጃ ወላጆች ማወቅ አለባቸው።

## ክፍል ሁለት፡- ወላጆች የቤተሰቡን አባላት የእርስበርስ ግንኙነትን እንዴት መልካም ማድረግ ይችላሉ?

የተመደበው ጊዜ **60** ደቂቃ

የቤተሰብ ግንኙነት ግንባታ

የቤተሰብ ግንኙነት ግንባታ የሚጀምረው ከጨቅላነት እድሜ ሲሆን ጨቅላ ህፃናት በአካባቢያቸው ስላሉ ሰዎች ለማወቅ የስሜት አካላቸውን ይጠቀማሉ። በተለያዩ ነገሮች ላይ በአይናቸው ትኩረት መስጠት ይጀምራሉ። የወላጆቻቸውን ወይንም የአሳዳጊዎቻቸውን ድምፅ፣ ዳሰሳ እንዲሁም ጠረን ይለማመዳሉ።

እድሜ በወራት እየጨመረ ሲመጣ የህፃናት ፈገግታዎች፣ የመገረም ድምፅና ማጉረምረም የቅርብ ግንኙነትን ለመመስረትና ለማሳደግ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። ቀስ በቀስ ከማህበራዊ ግንኙነት እርካታን ለማግኘት ስሜታቸውን መቆጣጠርና መምራት እንዳለባቸው ግንዛቤያቸውን ያሳድጋሉ። ስለዚህ የቤተሰብ መልካም ግንኙነት ግንባታ የሚጀምረው ከጨቅላነት ሲሆን በየእድሜ ደረጃው ክትትል እና ድጋፍ ይጠይቃል

ወላጆች ጤናማ የቤተሰብ ግንኙነት ለመመስረት ምን ማድረግ ይችላሉ

የቤተሰብ አባላት ግንኙነትን መልካም ማድረግ

- ❖ ቤተሰብ ህፃናት በራሳቸው ደህንነት የሚሰማቸው፣ ከፍርሀት ነፃ እና ደስተኛ የሚሆኑበት መሆን አለበት።

  የቤተሰብ አባላት እርስ በእርሳቸው በሚያደርጉት ቀጣይ ግንኙነት ለሌሎች አርአያ በመሆን ህፃናት በአለም ውስጥ እንዴት መንቀሳቀስ እንዳለባቸው ያስተምራሉ። መልካም የቤተሰብ ግንኙነት እንዲኖር አባወራዎች/እማወራዎች ለሁሉም የቤተሰብ አባላት ፍቅርና ደስታ መስጠታቸውን

አወያይ

መልካም

ዛሬ ባለ

ማግኘት

ሌላ ተ

መስራት

በጋራ በ

ስፍራዎ

ልምድ የ

አወያይ

ወላጆች በቤተሰብ አባላት መካከል ያለው ግንኙነት መልካም መሆኑን መከታተልና አስፈላጊ ማበረታታትን ወይንም እርማትን ማድረግ ይኖርባቸዋል።

መልካም የቤተሰብ ግንኙነት ባለበት የቤተሰቡ አባላት እርበርስ ይተሳሰባሉ ይደጋገፋሉ።

ለልጆቻችሁ የተወሰኑ ልዩ ጊዜዎችን መስጠት ከእነርሱ ጋር ጥብቅ ትስስር ለመፍጠር ይረዳል። ለምሳሌ ለእያንዳንዱ ልጅ አንድ ሰአት አብሮ ለመስራት፤አብሮ ለማንበብ ወይም ለሆነ ለልጅ ስሜት በሚሰጥ ስራ ለመመደብ ብትሞክሩ እያንዳንዱ ልጅ በዚያች ጊዜ አብሮአችሁ ለመሆን ይፈልጋል። ልጆች ይህቺን ሰአት እንዴት በጋራ ማሳለፍ እንዳለባችሁ በመወሰን እንዲሳተፉ ቅድሚያ ስጧቸው/አማራጭ አቅርቡላቸው። ለምሳሌ፡ መፃህፍት ማንበብ፣ መዝሙር መዘመር፣ በእግር ሽርሽር መሄድ፣ ጨዋታ መጫወትና ሌሎች ልጆች የሚያስደስታቸውን ነገር ማድረግ ትችላላችሁ። ከልጆቻችሁ ጋር ይበልጥ ተጨማሪ ጊዜ ባሳለፋችሁ መጠን ግንኙነታችሁ ጠንካራ ይሆናል።

አወያይ

መልካም ቤተሰቦች የመተማመን ጠቀሜታን ይገነዘባሉ። መተማመን ግንኙነት ጸንቶ እንዲቆይ የሚያያይዝ ማጣበቂያ ነው። በቤተሰብ ውስጥ መተማመንን የሚያሳድጉ ጥቂት ዘዴዎች፡

ልጆቻችሁ እምነታችሁን የሚያገኙበት አጋጣሚዎች ፍጠሩ። ለምሳሌ ለልጆች በቤት ዙሪያ ቀላል ተግባር እንዲያከናውኑ በማድረግ በራሳቸው ሲያከናውኗቸው አመስግኗቸው።

ለልጆቻችሁ እንደምትወዷቸውና እንደምታከብሯቸው፤እንደምትተማመኑባቸው ግለፁላቸው። ህፃናት ወላጆቻቸው ሲያደንቋቸው በተነገራቸው መሰረት ተግባራትን ስለማከናወናቸው ወይም መልካም ጠባይ ለማሳየት  ይተጋሉ።

ልታደርጉ የማትችሉትን ነገር ቃል አትግቡ።  ልታደርጉላቸው ቃል የገባችሁትን ነገር ተከታትላችሁ አድርጉላቸው።

የቤተሰብ አባላት ሰዎች እስከሆኑ ድረስ እንደሚሳሳቱ ማሳወቅ ይገባል። በተጨማሪም ስህተት በይቅርታ መታለፍ እንደሚቻል ማሳወቅ ተገቢ ነው። ለልጆቻችሁ ይቅር ማለትን አስተምሯቸው። እናንተም እርስ በርስ ይቅርታ መጠየቅንና ይቅር መባባልን በተግባር አሳዩ።

መልካም ግንኙነት ባለበት ቤተሰብ ቅሬታ ሲኖር በሰላማዊ መንገድ በግልፅ ውይይት ይፈታል። ነገርን በሆድ አቆይቶ ወደ ቂመኝነት መሄድ ስህተት ነው።

ያለፈው በደል ላይ ማተኮር ተጨማሪ ጉዳት እንጂ ጥቅም እንደሌለው መግለፅ አስፈላጊ ነው።

እያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ይቅርታ!   ያሳዝናል!   የሚሉትን በአግባቡ ተግባር ላይ ማዋልን አስተምሩ። ለመጥፎም ይሁን ለመልካም ጠባያት ሀላፊነት መውሰድ አስፈላጊ በመሆኑ የቤተሰብ አባላት ለሚያደርጉት ነገር ራሳቸውን ሀላፊና ተጠያቂ ማድረግን አባወራዎች/እማወራዎች በአርአያነት ያስተምሩ። ይህ መተማመንን ለማሳደግ ይረዳል።

አወያይ

በሁሉም ቤተሰቦች ውስጥ ግጭት ይፈጠራል። ግጭት በሰዎች ግንኙነት ውስጥ የሚከሰት ተፈጥሯዊ ሂደት ነው።

ጠንካራ ቤተሰቦች በግጭትና በአለመስማማት ወቅት ትኩረታቸውን ከግለሰብ ይልቅ ችግሩ ላይ አድርገው ይሰራሉ። በሌላ አነጋገር መልካም ቤተሰቦች በእርስ በርስ አለመስማማት ጊዜ ለማተኮር የሚሞክሩት በተባለው ነገር ወይንም በተደረገው ድርጊት ላይ እንጂ በተናጋሪው ወይንም ጉዳዩን በፈፀመው ሰው ላይ አይደለም። ይህ አቀራረብ ግጭቶች እንዳይባባሱ፤ ይልቁኑም በቀላሉ ስምምነት እንዲፈጠር ፍቱን ዘዴ ነው።

የሆነ ግጭት ሲፈጠር ድሮ የሆኑ ጉዳዮችን ወይንም ችግሮችን በማንሳት ፀብ እንዲጋጋል ከማድረግ ውጪ ጥቅም የለውም። ያለፉ ጉዳዮችን ወይንም ችግሮችን ማንሳት ከወቅታዊው ጉዳይ እንድንሸሽ ያደርገናል።

ወላጆች ግጭቶች ወደ ሁከት እንዳያመሩ ከቤተሰብ አባላት ጋር መወያየት ያስፈልጋቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ወላጆች በጣም ተበሳጭተው ያበሳጫቸውን ወይም ያገኙትን የቤተሰብ አባል/ ልጆችን ሊደበድቡ ወይንም እቃ ሊወረውሩባቸው ይችላሉ። ይህ ድርጊት የተፈጠረውን ችግር ከመፍታት ይልቅ ችግሩን የሚያባብስና ሌሎች ተጨማሪ ችግሮችን የሚፈጥር ስለሆነ ተቀባይነት ያለው የችግር መፍቻ መንገድ አይደለም።

ስለሆነም ወላጆች ራሳቸውን አርአያ በማድረግ የቤተሰብ አባላት ተረጋግተው በውይይት ላይ እንዲያተኩሩ መምከር ይኖርባቸዋል። ያልተፈለገ ጠባይን በተመለከተ ህፃናትን በውይይት ባሳተፍናቸው መጠን የተሻሉ የርስበርስ ግንኙነቶችን እዳበሩ ያድጋሉ።

ሁብረተሰብ የሚፈጠረው ከተለያዩ ዳራዎች (ባህል፣ቋንቋ፣ሀይማኖት፣ብሄር፣የኑሮ ደረጃ፣የትምህርት ደረጃ፣ ወዘተ) በሚመጡ ህዝቦች ነው። ሰላማዊ ሁብረተሰብ ይኖረን ዘንድ ከተለያዩ ዳራዎች የሚመጡ ህዝቦችን ማክበር ይገባናል። ይህም ከተለያዩ ዳራዎች ከሚመጡ ህዝቦች ጋር ለመኖር ያስችላል።

ስለዚህም ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች ልጆች በህዝቦች መካከል ያሉ ልዩነቶችን እንዲቀበሉ አጋጣሚዎችን መፍጠር ይገባቸዋል። ይህን ግንዛቤ በቤተሰብ አባላት መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ የአስተሳሰብና የፍላጎት ልዩነቶችን መሰረት በማድረግ ልጆችን ማለማመድ ይቻላል። ማለትም ባንስማማበትም አንዳችን የሌላውን የቤተሰብ አባል አስተሳሰብና ፍላጎት ማክበርን ወላጅ አርአያ በመሆን ልጆችን ማስተማርና ማበረታታት ማለት ነው።

ራስንና የራስ የሆነውን ማክበር አስፈላጊ ስለመሆኑ እንዲሁም ሌሎችን እና ሌሎቹ የኛ ነው የሚሉትን ሁሉ ማክበር እንደሚያስፈልግ አርአያ ሆነው ለልጆች ማለማመድ ያስፈልጋል።

ወላጆች ሌሎችን በማክበር እንዲሁም የተለያየ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሰዎች በመንከባከብ አርአያ መሆን አለባቸው።

በባህላችን የተለመደውን የሴት ልጅ ጥቃት ለመቀነስ ወንዶች ልጆች የልጃገረዶችንና ሴት ልጆችን መብት እንዲያከብሩ ማስተማር ይገባል። ይህንን ለማስተማር አባቶችና ትላልቅ ወንዶች ሴቶች ላይ ጥቃት ከመሰንዘር በመታቀብ ምሳሌ መሆን አለባቸው።

ለልጆች ከተለያዩ ብሄር፣ ባህሎችና ሃይማኖቶች የመጡ ሰዎችን እንዲያከብሩ ማስተማር አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም አንዳንድ ህፃናት ምን ያህል ጥቃት እየደረሰባቸው እንደሆነ ማስተማር ይገባል። ወላጆች ወይንም ሞግዚቶች ልጆቻቸው የአካል ጉዳት ምንነትን እንዲያውቁ በማድረግ እንዲሁም ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ልጆች በማጠናከር በጨዋታዎችና በተለያዩ ተግባራት እንዲያሳትፏቸው ሊያበረታቷቸው ይገባል።

## 5. ወንዶች እና ሴቶች ልጆችን እኩል መመልከት

አወያይ

በቤተሰብ አባለት መካከል በሚኖረው ግንኙነት ወንዶችና ሴቶች ልጆችን በእኩልና በተመሳሳይ ሁኔታ መመልከት ተገቢ ነው። ለምሳሌ፡ በቤት ውስጥ በፅዳትና በምግብ ዝግጅት ወንዶችና ሴቶች ልጆችን እኩል ማሳተፍ አስፈላጊ ነው። ሴቶች ልጆች በተለምዶ ለወንዶች ልጆች ብቻ በተሰጡ ስራዎች እንዲሁም በተቃራኒው ባሉ ስራዎች ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ ይገባል። በቤተሰብ ውስጥ አዋቂ ወንዶችና ሴቶች ለህፃናት አርአያ በመሆን በቤት ስራ እርስ በእርሳቸው መረዳዳት አለባቸው።

ህፃናት መካከል መልካም የቤተሰብ ርስበርስ ግንኙነት ግንዛቤና ልምድ

እንዴት ይገነባል?

ሀ) ህፃናት የወላጆቻቸውን ወይንም የሞግዚቶቻቸውን ዳሰሳ እንዲሁም ጠረን ይለማመዳሉ፡ይህንንም በመጠቀም ራሳቸውን ከቤተሰባቸው ጋር ለማዛመድ ይሞክራሉ።

ለ) ቀስ በቀስ ህፃናት በጨዋታ ከትላልቅ ልጆችና ከወላጆች/ከአሳዳጊዎች ጋር ግንኙነት ይመሰርታሉ

ሐ) ከአንድ እስከ ሁለት አመት እድሜ ያላቸው ህፃናት ግንኙነታቸውን የሚያጠናክሩት በጨዋታ ነው።

አወያይ

ህፃናት ስለአካባቢያቸው ለማወቅ ጉጉት አላቸው። በህይወታቸው መጀመሪያ ህፃናት የሚኖሩበትን አለም ለማወቅ አይኖቻቸውን፣ ቆዳቸውን፣ አፍንጫቸውንና አፋቸውን ይጠቀማሉ። ህፃናት በስሜት አካላቸው ስለ አለም ይማራሉ። በተለያዩ ነገሮች ላይ በአይናቸው ትኩረት መስጠት ይጀምራሉ።

አወያይ

ልጆች በጊዜ ሂደት የቅርብ ግንኙነትን አስደሳችነት ይማራሉ። የህፃናት ፈገግታዎች፣ የመገረም ድምፅና ማጉረምረም የቅርብ ግንኙነትን ለመመስረትና ለማሳደግ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ።

በጨዋታ ጊዜ ወላጆች ወይንም ሞግዚቶች የፍቅርና የእንክብካቤ ቅላፄ ያለውን ድምፅና ዜማ ለመጠቀም መሞከር አለባቸው።

መ) ከሁለት እስከ ሶስት አመት እድሜ ያላቸው ደግሞ ከቤተሰብ አባላት ጋር የሚግባቡባቸውን የቃላት ቁጥር በጣም ያሳድጋሉ። እንዲሁም ከማን ጋር ሲሆኑ ምን አይነት ስሜት እንደሚሰማቸው ይገነዘባሉ፤ በዚህም የተነሳ ከቤተሰቡ ውስጥ ለተለያዩ ሰዎች የተለያየ ቀረቤታ ያሳያሉ።

ሠ) ከአራት እስከ አምስት አመት እድሜ ያላቸው ህፃናት ስለሌሎች የተሰማቸውን በትክክል የማንፀባረቅ ችሎታ ይኖራቸዋል። በተጨማሪም በእርስበርስ ግንኙነት ተቀባይነት ለማግኘት ስሜታቸውን መቆጣጠርና መምራት እንዳለባቸው ግንዛቤያቸውን ያሳድጋሉ።

የቤተሰብ የርስበርስ ግንኙነትን በተመለከተ ሰለግል ግንዛቤ የጋራ ውይይት

> አወያይ
>
> በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በመመርኮዝ ተሞክሯቸውን እንዲናገሩ ተሳታፊዎችን ያበረታቱ። ከፍቃደኞች ውስጥ ለሶስት ተሳታፊዎች እድሉን ይስጡ።

ለውይይቱ ተሳታፊዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎች

ሀ. ከምታውቋቸው ቤተሰቦች ውስጥ በቤተሰብ አባላት መካከል የሚታዩ ለህፃናት እድገት ጠቃሚ ግንኙነቶች ምንድን ናቸው?

ለ. በምታውቋቸው ቤተሰቦች ውስጥ በቤተሰብ አባላት መካከል የሚታዩ ለህፃናት እድገት ጠቃሚ ያልሆኑ ግንኙነቶች ምንድን ናቸው?

የተግባር ልምምድ፦ የቡድን ውይይት

አወያይ

ተሳታፊዎች በአጫጭር ታሪኮች ላይ ተመርኩዘው ለሚቀርቡላቸው ጥቄዎች በጋራ ተወያይተው መልስ እንዲሰጡ ይጠበቃል፡ተሳታፊዎችን በሶስት ቡድን ይክፈሉ።
ለሶስቱም ቡድን ለእያንዳንዳቸው ገጠመኝ የተፃፈባቸው ሁለት ገፅ ወረቀቶች ይሰጣቸው።
ለቡድኑ አባላት እያንዳንዱን ገጠመኝ በተመለከተ የቀረቡትን ጥያቄዎች መመለስ እንዳለባቸውና ጥያቄውን ለመመለስም በታሪኩ ላይ በቡድናቸው መወያየት እንዳለባቸው ይነገራቸው።
የእያንዳንዱን ቡድን ውይይት የሚመሩ ሰዎች ሊኖራቸው እንደሚገባ ይገለፅላቸው። ከተሳታፊዎች መካከል የውይይቱን ጭብጥ የሚፅፉና ለሁሉም ተሳታፊዎች የሚያቀርቡ ሰዎችን በማስመረጥ በተሳታፊዎች የሚሰጡ መልሶችን እንዲዘግቡ ያድርጉ።

ለተሳ

1. በገጠመኙ ውስጥ በቀረቡት የቤተሰብ አባላት መካከል ያለው ግንኙነት ለህፃናት እድገት ጥሩ ነው ወይስ መጥፎ ነው? ለምን?
2. በገጠመኙ ውስጥ በቀረቡት ወላጆችና ልጆች መካከል ያለው ግንኙነት ለህፃናት እድገት ጥሩ ነው ወይንስ መጥፎ ነው? ለምን?
3. በገጠመኙ ውስጥ የቀረቡት ወላጆች በመካከላቸው ያለው ግንኙነት ሁኔታ መልካም እንዲደርጉና የልጆቻቸውን እድገት ለማገዝ ምን እንዲያደርጉ ትመክሯቸዋላችሁ?

በገጠመኙ ውስጥ የቀረቡት ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ሁኔታ እንዲለውጡና የልጆቻቸውን እድገት ለማገዝ ምን እንዲያደርጉ ትመክሯቸዋላችሁ?

<u>ታሪክ አንድ- አቶ ማሞና ልጆቻቸው</u>

አቶ ማሞ የስድስት ልጆች አባት ናቸው። አቶ ማሞ ስራ በጣም ስለሚበዛባቸው እረፍት የላቸውም። በየእለቱ ልጆቻቸው ከመኝታቸው ሳይነቁ ወደ ስራቸው ይሄዳሉ። ማታ ደግሞ ልጆቹ ከተኙ በኋላ ከምሽቱ ሶስት ሰአት ላይ ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ። አቶ ማሞ ዘወትር ለቤተሰቦቻቸው ጊዜ መስጠት ባለመቻላቸው የጥፋተኝነት ስሜት ይሰማቸዋል።

የአቶ ማሞ ልጆች እናታቸውን ወደ ተለያዩ ቦታዎች ለምሳሌ ወደ ገበያ፣ ወደ ወንዝ፣ ወደ ሜዳ፣ በአቅራቢያቸው ወደ ሚገኘው መንደር እንዲሁም ራቅ ብለው አያቶቻቸውንና ዘመዶቻቸውን ለመጎብኘት እንዲወስዷቸው በተደጋጋሚ ይጠይቃሉ። ይሁን እንጂ እናታቸው በቤት ውስጥ ስራ ፋታ ስለሌላቸው ይህንን ማድረግ የሚችሉት አባታቸው አቶ ማሞ ብቻ መሆኑን ትነግራቸዋለች። አቶ ማሞ የልጆቹን ፍላጎት ማሟላት ባለመቻለቸውና

ለልጆቹ ጊዜ ስለሌላቸው ልጆቹ ብዙ አይወዷቸውም። አይቀርቧቸውም። አቶ ማሞ አንድንድ ጊዜ በአጋጣሚ ጥቂት ጊዜ አግኝተው ከልጆቹ ጋር መጫወት ሲፈልጉ እንኳ ልጆቹ ቤት ውስጥ ቆይተው ከአባታቸው ጋር ከሚጫወቱ ይልቅ ወደ ውጪ በመውጣት ከሰፈር ልጆች ጋር መሆን ይመርጣሉ። በዚህ የተነሳ አቶ ማሞ ልጆቻቸውን መጥላት ጀምረዋል። በቤት ውስጥ ሲሆኑም በጣም ብቸኝነት ይሰማቸዋል።

<u>*ታሪክ ሁለት- ዘመዴ*</u>

ዘመዴ የሰባት አመት ልጅ ስትሆን የአንደኛ ክፍል ተማሪ ናት። ብዙውን ጊዜ ከጓደኞቿ ጋር ስትወዳደር በጨዋታ ደስተኛ አይደለችም። በተጨማሪም ጠንካራ አይደለችም። ወላጆቿ ብዙ ጊዜ እርሷ ፊት ይጨቃጨቃሉ። ዘወትር አባቷ እናቷን ሲደበድቡ ታያለች። ዘመዴ በተደጋጋሚ ያለምክንያት ትጮሃለች። ነገር ግን አባቷም ይሁኑ እናቷ አያባብሏትም። ወይንም ለምን እንደምታለቅስ አይጠይቋትም። ይልቁንም እናቷ ለአባቷ ‹ይቺን ልጅ ዝም አሰኟት› ይሏቸዋል። አባቷም ዘመዴ ላይ በመጮህ ማልቀሷን ካላቆመች በቀበቶ እንደሚገርፏት ያስፈራሯታል። ዘመዴ የአባቷን ጩኸትና ማስፈራራት በመፍራት በጣም ታለቅሳለች። በዚህን ጊዜ አባቷ ድብደባ ይጀምራሉ። አባቷ በጠንካራ እጆቻቸው ይዘዋት በቀበቶ ወይም በአርጩሜ ይገርፏታል። በዚህ የተነሳ ዘመዴ አባቷን በጣም ትፈራለች። አባቷ ወደ ቤት መግባታቸውን ስትሰማ ሮጣ ወደ ጓሮ ትሄዳለች። ዘመዴ ቤት ውስጥ ስትሆን ደግሞ ወደ አባቷ አጠገብ አትደርስም። ይልቁንም በማእድ ቤት እናቷን ትከተላለች። ዘመዴ ወደ ውጪ ወጥታ ከጎረቤት ልጆች ጋር ለመጫወት ፈቃድ ስትጠይቅ እናቷ ይህንን ጥያቄ ካላቆመች

ለአባቷ እንደምትናገርባት ታስፈራራታለች። ስለዚህም ዘመዴ ብዙ ጊዜ ባልታወቀ ምክንያት ከማልቀሷ በስተቀር ዝም ብላ ትቀመጣለች። ዘመዴ በማታለቅስበት ጊዜ  ስራ እንድትሰራ በእናቷ ካልታዘዘች በስተቀር ጓሮ በአንድ ጥግ ዝም ብላ ትቀመጣለች።

*የጋራ ውይይት ዘገባና ውይይት* **(***ሃያ ደቂቃ***)**

*አወያይ*

*ለእያንዳንዱ ቡድን  ተወካይ ሶስት ደቂቃ ብቻ በመፍቀድ የየቡድናቸውን መልስ እንዲያቀርቡ ያድርጉ*

*ተወካዮች ካቀረቡ በኋላ ደግሞ ሁለት  ተሳታፊዎች አስተያየት እንዲሰጡ ወይንም ጥያቄ  እንዲያቀርቡ ያድርጉ።*

*አወያይ፡ ተወካዮች ባቀረቡት ወይም በተሰጡ አስተያየቶች ላይ እርማት መስጠት ወይም ሀሳቡን ማጠናከር ይኖርበታል።*

## ቁልፍ መልእክቶች

- የቤተሰብ አባላት በምግብ ሰአት ከሚደረገው መገናኘት ተጨማሪ የአብሮነት ጊዜ ያስፈልጋል።  ይህም የቤተሰብ አባላት እርስ በእርስ ልምድ እንዲለዋወጡና እንዲገናኙ ያስችላል። በቤት ውስጥ ወይም በግቢ

የሚሰሩ ስራዎችን አብሮ በመስራት ወይም አንዱ ሲሰራ ሌላው አብሮ በመሆን፤ ለውይይት ወይም ለጋራ ጨዋታና ለሽርሽር መርሐ ግብር ማውጣት ያስፈልጋል።

- በቤተሰብ ውስጥ አንዱ ስለሌላው መልካም ቃላትንና ሙገሳዎችን የመለዋወጥ ባህል ማዳበር
- በቤተሰብ አባላት መካከል ግጭትን በግልጽ ውይይትና አንዱ የሌላውን አቋም በማክበርና ከጥላቻ በራቀ ሰላማዊ ሁኔታ በመነጋገር መፍታት አስፈላጊ ነው። በተናጋሪው ሳይሆን በተነሳው ጉዳይ ላይ ማተኮር።
- ለወንዶችና ለሴቶች ልጆች እኩል እንክብካቤ መስጠት። በተጨማሪም ከሁለቱም ፆታዎች ተመሳሳይ ነገር መጠበቅ (በቤት ስራ፣ በትምህርት፣ ወዘተ)።
- ልጆች እድሜያቸው ሁለት አመት ተኩል ሲሆን ጀምሮ ጥቃቅን እቃዎችን ከማቀበል ጀምሮ ቀስ በቀስ በቤት ውስጥ ስራዎች በመሳተፍ ለቤተሰብ ማገልገልን መማር ይችላሉ። ስለዚህ ወላጆች እዚህ ላይ ትኩረት አድርገው በፍቅር ነገር ግን በጥብቅ አመራር ህፃናት ለቤተሰቡ አስተዋፅኦ የማድረግን ባህሉን እንዲያዳብሩ ማሰልጠን ይኖርባቸዋል።
- ጨቅላ ህፃናት በአካባቢያቸው ስላሉ ሰዎች ለማወቅ የሚጠቀሙት አይናቸውን፣ ቆዳቸውን፣ አፍንጫቸውንና አፋቸውን ነው። ስለዚህም ወላጆች ወይንም ሞግዚቶች ከህፃናቱ ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ለማጠናከር የህፃናቱን የስሜት አካላት መሰረት ማድረግ ያስፈልጋል።
- ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች ከህፃናት ጋር ጨዋታዊ ግንኙነት ለመመስረት ወይንም ለማጠናከር የፍቅርና የእንክብካቤ ቅላፄ ያለው ድምፅ መጠቀሙ ፋይዳው ጉልህ ነው።
- ለልጆችዎ ሙሉ ትኩረት በመስጠት ያዳምጧቸው። ሁሉም የቤተሰብ አባላት ሀሳባቸውንና ስሜታቸውን በነፃነት እንዲያጋሩ ማበረታታት።
- ለልጆቻችሁ የተለየ ጊዜ (የሚያስደስትና ግንኙነትን የበለጠ የሚያጠናክር) ይስጡ። ይህም ከልጆች ጋር ጥብቅ ግንኙነት ለመመስረት ይረዳል።
- ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነትን በመፈተሽ ችግሮችን ማረምና መልካም ግንኙነትን ማስቀጠል አለባቸው።
- በማህበረሰባችን ውስጥ በህፃናት እንክብካቤ ጎረቤቶች በጣም አስፈላጊ ናቸው። ጎረቤቶች በህፃናት እንክብካቤ ከፍተኛ ድጋፍ ማድረግ ይችላሉ። ከጎረቤቶቻችን ጋር መልካም ግንኙነት መመስረት የህፃናት እንክብካቤ ሀላፊነትን ለማካፈል ይጠቅማል። ነገር ግን የጎረቤቶቻችንን ጠባይ ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል።

አወያይ

ለልጆች መልካም አስተዳደግ ወሳኝ የሆነውን መልካም የቤተሰብ አባላት የርስበርስ ግንኙነትን ለልጆች የማመቻቸትና ልጆቹ ከሚገናኟቸው ሰዎች አስፈላጊውን እንክብካቤና ግንዛቤ የሚያገኙ መሆኑን ማረጋገጥ የወላጆች ወይንም የአሳዳጊዎች ሀላፊነት ነው።

ለብዙ አመታት መልካም ያልሆነ ግንኙነት ሳይኖራቸው ያደጉ ህፃናት ከፍ ሲሉ ከሌሎች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ደህንነት አይሰማቸውም።

በቤተሰባችን አባላት መካከል ያሉትን ግንኙነቶች እንዴት መገምገም እንችላለን**?**

ወላጆች እርስ በርስም ሆነ ከልጆቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት በመገምገም ማረም ያስፈልጋቸዋል።

ቤተሰብ ውስጥ ባሉ አዋቂዎች መካከል ወይም ከልጆች ጋር መግባባትን ማስፈን ያቃተው የቤተሰብ አባል በቤተሰቡ ውስጥ ትልቅ ነገር እንደጎደለው ሊሰማው ይችላል። በዚህ ወቀት ግለሰቡ ከቤተሰቡ መራቅ ሊጀምር ይችላል። ለምሳሌ ለምሳሌ ውጪ መመገብን፣ ሰበብ እየፈጠሩ ከቤት መውጣትን፣ አብዛኛውን የእረፍት ጊዜውን ከጓደኞች ጋር ከቤት ውጪ መጫወትን ወይንም ጊዜን በመጠጥ ቤት ማሳለፍን ልማድ ሊያደርግ ይችላል። እነኚህ ያልተለመዱ ምልክቶች ከታዩ ይበልጥ የቤተሰቡን መልካም ግንኙነት እንደሚሻክሩና ለልጅ መልካም አስተዳደግ ጠንቅ መሆናቸው ታውቆ እራስን ከመሰል ድርጊቶች መቆጠብ መልካም ነው። በምትኩ ራስንና የቤተሰቡን ሁኔታ በመገምገም መጥፎ ስሜት ስለፈጠረብን ጉዳይ ከቤተሰብ ጋር በመነጋገር መፍትሄ እንዲገኝ በግልጽ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።

በቤተሰቤ ውስጥ ያለው ግንኙነት መልካም አይደለም ብለው ከገመገሙ ግልጽና መከባበር የተሞላበት ውይይት በማድረግ ነገሮችን ለማስተካከል እርምጃ መውሰድ ። መፍትሄ ማግኘት ካልተቻለ በአካባቢያቸው የሚገኙ ባለሙያዎችን ማማከር ያስፈልጋል።